# ይመስገን ፈጣሪ!!



ኢትዮጵያን ስቃኛት ፥ ቀና ብዬ ሳያት፣

ብርሃኗን ስትሰጥ፥ እኔ መቼ አየኋት፣

ደመና ከልልዋት ፥ ከጉም ውስጥ ገብታ፣

እኔ በፍለጋ ስዋትት ሁል ግዜ፥ ጠዋትና ማታ፣

ጉልበቴን ጨርሳ ፥ እኔን አኮራምታ ፣

ከጭንቅ ውስጥ ከታኝ፥ ውልቅ ብላ ወጥታ፣

ለመድረስ ስቃትት እጆቼን ዘርግቼ፣ ዓመታት ቆጠርኩኝ ትመጣለች ብዬ፣

የጨለማን ጉዞ መንገድሽ አድርገሽ ፣የብርሃን እናት የኔ ከለላዬ፣

አዝግማ እየሄደች ፥ በምህዋር ውስጥ ገብታ፣

ፍትሕና ርትዕ፥ ከቤቷ ውስጥ አጥታ፣

መስዋት ተከፍሎልሽ፥ ስንቱ ሕይወቱን ሰጥቶ፣

በብርድ በቁሩ ፥ አደባባይ ወጥቶ፣

ላንቺ የጮኸልሽ፥ ድምጹን አሰምቶ፣

መናኩስት ሳይቀሩ ፥ የፍጥኝ ታግቶ፣

ሼኩ እምቢ ብለው ፣ ከስር ቤት ውስጥ ገብተው፣

ድምጻችን ይሰማ ፥ እያሉ ተማጉተው፤

ይኸው  ኢትዮጵያዬ፥ አሁን ለዚህ ደርሰን፤

ለሃያ ሰባት ዓመት፥ ከኛ ተሰውራ፤

ውርደት አከናንበው፥ ስሟ እንዳይጠራ፤

አሁን ብርሃን ሰጠች፥ ታየች አሉ ደምቃ፤

ሆ ብሎ ሲነሳ ፥ ህዝቡ ያለው ቃና፤

ለኔ የሰጠው ደስታ፥ ይድረስ ለፈጣሪ ትልቁ ምስጋና፤

ሁሌም ትኖሪያለሽ ፥ እንዲህ እያበራሽ፤

እንደድር አብረሽ ፥ በፍቅር ተሳስረሽ፤

ለድሃው ደግፈሽ፤ ለታመመው ደርሰሽ፤

መይሳው ከምድረ ስዊድን

2018-12-08